ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን *

ቅጽ 43፤ ቁ.1 ኅዳር፤ 2008

# የድርቅ ወሬ በዘመነ "ልማታዊ መንግሥት"?

በአየር ንብረት መዛባት ምክንያት በርካታ የዓለም አገሮች የምግብ እጥረት እንደሚያጋጥማቸው የታወቀ ነው። ሆኖም፣ ችግሩ ያንዣበበባቸው አገሮች መንግሥታት ሁኔታውን አስቀድመው በመገንዘብ ጠንካራ ርብርቦሽ በማድረግ በጣም አነስተኛ ወይም ምንም ጉዳት ሳይደርስ ሕዝባቸውን ድርቅ ሊያስከትል ከሚችለው አደጋ ይከላከላሉ። ችግሩን ለመቋቋም የሚወስዷቸው እርምጃዎች ሁኔታው ከመባባሱ በፊት የእህል ጎተራ ሠርቶ እህል በማከማቸት፣ መኪና መንገድ ባልገባባቸው አካባቢዎች መንገድ በመሥራት፣ ችግሩ በተፈጠረበት አካባቢ በቂ የውኃ አቅርቦት በማድረግ፣ በአጠቃላይም፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ ቅድመ-ዝግጅት በማድረግ ነው። ከአንዳንድ አገሮች እንደምንማረው፣ በአገራቸው ውስጥ የምርት እጥረት ካለ በቂ ምርት ካላቸው አገሮች ገዝተው ለሕዝባቸው በማቅረብ የጎደለውን ያሟላሉ። "ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" እንደሚባለው የዐረብ አገሮች በአገራችን ውስጥ እህል እያመረቱ ምርቱን ወደ አገራቸው የሚያጓጉዙት ሕዝባቸውን ለመመገብ ነው።

አለመታደል ሆኖ በአገራችን ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ዝግጅቶች ከማድረግ ይልቅ በሥልጣን ያሉትና የነበሩት አምባገነን አገዛዞች ትኩረታቸው በሥልጣን ላይ መቆየት ብቻ በመሆኑ በተከታታይ ጊዜያት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝባችን እንደቅጠል ሲረግፍ፣ አላየነም፤ አልሰማም ብለዋል። አሁንም ይኸው እየታየ ነው። የአሁኖቹማ ይባስ ብለው አገሪቱ በልማት እየገሰገሰች ነው፤ ሕዝባችንንም በቀን ሦስት ጊዜ እንዲበላ አስችለነዋል

እያሉ ነጋ ጠባ በቁጥጥራቸው ሥር ባሉት የመገናኛ ብዙኃን አካኪ ዘራፍ እያሉ ባሉበት ወቅት ነው 8.3 ሚሊዮን ሕዝብ ለችግር መጋለጡን የዓለም የዕርዳታ ድርጅቶች የዘገቡት። አገዛዙም የዓለም አቀፍ የዕርዳታ ድርጅቶች ሁኔታውን ለዓለም ይፋ ካደረጉ በኋላ ነው እውነታውን ለመቀበል የተገደደው።

በአንዲት አገር ውስጥ ረሀብ የሚከሰትበት አንደኛው ምክንያት በተፈጥሮ የአየር መዛባት ምክንያት ዝናብ ሲጠፋ ነው። ይህ ዓይነቱ ረሀብ በከፍተኛ ደረጃ የሰውንና የእንሰሳትን ሕይወት የሚያወድም አስፈሪና አሰቃቂ ክስተት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከመልካም አስተዳደር እጦት በሚመጣ የኤኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሲሆን፣ የሚያጠቃውም በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደረውን የመጨረሻውን ድኃ የኅብረተሰብ ክፍል ነው።

አለመታደል ሆኖ በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለቱም ዓይነት ችግሮች ኅብረተሰባችንን እየጠበሱት ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ በኑሮ ውድነት ምክንያት በከተማ ውስጥ እህል ሸምተው ቤተሰባቸውንና እራሳቸውን መመገብ ያቃታቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እጅግ በጣም በርካታ ሆነዋል። ልጆቻቸውም ዕለት ከዕለት በረሀብ አለንጋ በመጠበሳቸው ምክንያት ትምህርት መማር እንዳልቻሉ ተደጋገሚ ዘገባዎች ይፋ አድርገውታል። ይህንን ሁኔታ የተገነዘቡ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶችም ከተማ ውስጥ የዕርዳታ ስንዴና አልባሳት ያከፋፈሉበት ወቅት እንዳለ ተስተውሏል። የድኃ ልጆች በረሃብ ጠኔ ተይዘው በጣረ ሞት አፋፍ ላይ በሚኖሩባት በዋና ከተማችን በአዲስ አበባ ውስጥ በአንፃሩ ደግሞ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ ባለሥልጣኖች ልጆች ምግብ አትረፍርፈው ይደፉሉ። ባለፀጎችም የሀፍረተ-ቢስ ካባቸውን አጥልቀው ይህንን ዘግናኝ ሁኔታ አላየንም፤ አልሰማንም፤ የትምክህተኞችና የአሸባሪዎች ወሬ ነው ከማለት ደርሰዋል።

ህወሓት/ኢህአዴግ በደርግ ዘመን ተከስቶ የነበረውን ረሀብ አስመልክቶ የደርግን መንግሥት ለማሸሟጠጥ ያወጣው ቪዲዮ እንደነበረ የሚታወስ ነው። ቪዲዮው የሚያሳየው የአገራችን ሕዝብ በረሀብ እየረገፈ የደርግ ባለሥልጣኖች በተለያዩ መናፈሻዎች እየተዝናኑ ምግብ በገፍ ቀርቦላቸው ሲበሉና ሲጠጡ የሚያሳይ ነበር። ከቪዲዮው ግርጌ እኛ ሥልጣን ስንይዝ ይህንን መከራ እንቀርፍልሃለንና ደግፈን፤ ተቀበለን የሚል ቅስቀሳ አስፍረውበት ነበር።

ታዲያ በአሁኑ ጊዜ ሕዝባችን በትግራይ፣ በአፋር፣ በወሎና በሲዳሞ እንደቅጠል እየረገፈ ባለበት ወቅት፣ የህወሓት የቀትር ጃንጥላ የሆነው አማራውን እወክላለሁ የሚለው ብአዴን (ብሄረ-አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) የተመሠረተበትን ዓመታዊ በዓል ለማክበር በሚሊዮን የሚገመት ወጪ መድቦ ሽር-ጉድ ማለቱ ምን ያህል ለሕዝብ ደንታ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ የአድርባዮች፣ የአጎብዳጆችና የአሽቃባጮች የባዶ ቡድን ጥርቅም መሆኑን ነው። ለነገሩማ "ውሻ ከጌታዋ ጋር እኩል ለመሆን ከዳር ተቀመጠች" እንደሚባለው ነው። የህወሓት/ኢህአዴግ ድርጅት በየዓመቱ እጅግ ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ የተመሠረተበትን ዓመት ስለሚያከብር ብአዴንም እንዳቅሚቲ ጌታውን ለመምሰል ፊነጠዘ፤ ሽር-ጉድ፣ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ።

በተለያዩ ጊዜያት፣ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ያለውን ጊዜ የማይሽረው ረሀብና ድርቅ በዓለም ሕዝብ ፊት የአገራችን የኢትዮጵያ ልዩ መታወቂያዋ ከሆነ እነሆ ግማሽ ምዕተ-ዓመት ሊሞላው ነው። በእነዚህ አሥርተ-ዓመታት ሁሉ፣ ድርቅ ሲባል ኢትዮጵያ፣ ረሀብ ሲባል ኢትዮጵያ፣ በየጊዜው በአጥንቱ የቀረ ረሀብተኛ ሲባል፣ በዓለም ዙሪያ በየድረ-ገጹ የኢትዮጵያዊ ምስል እየታየ መለያችን ሆኗል። ለምዕራቡ ዓለም ሕዝቦች ምስጋና ይግባቸውና በአገራችን ለተከሰተው የምግብ እጥረት እንዲሁም በሽታና ሞት በተቻላቸው ታድገውናል፤ አሁንም ቢሆን እየታደጉን ይገኛሉ።

እንዳለፉት መንግሥታት ድርቁን ከኢትዮጵያ ሕዝብና ከዓለም ሕዝብ ለመሸሸግ የዳዳው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ፣ አፍጥጦና አግጦ ሲመጣ ወደ ልመና በመግባት፣ በዘንድሮው ዓመት እስከ 8.2 ሚሊዮን የሚሆን የአገራችን ሕዝብ በጽኑ ረሀብ እንደሚማቅቅና ይባስ ብሎም በሚቀጥለው ዓመት የተጎጂው ሕዝብ ቁጥር ወደ 15 ሚሊዮን ከፍ ሊል እንደሚችል ገምቷል። የኢትዮጵያ መንግሥታት ዓይናቸውን በጨው ታጥበው ምጽዋት መጠየቅና ድርቁን መለመኛ ማድረግ ሙያ አድርገውት ኖረዋል። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝም $596 ሚሊዮን ብር በአስቸኳይ እንዲለገስለት ማስጠንቀቂያ ቢጤ ያለበት ልመና አቅርቧል። እንዲያውም የሀፍረተ-ቢሱ የህወሓት ሹማምንት የዓለም መንግሥታት ወደ ሶሪያ ስደተኞች ጥያቄ ፊታቸውን በማዞራቸው የልመና ሙዳያቸው ሊሞላ አይችል ይሆናል

እያሉ ሲማልሉ ተደምጠዋል። ይህ የ180 ዲግሪ መጠማዘዝ የተከሰተው ከጥቂት ወራት በፊት ሌሎች የህወሓት ባለሥልጣናት "የድርቁ መጠን ሰፊ አይደለም፤ በቂ እህልና ሰፊ ዝግጅት አለን" እያሉ በቀላመዱ ማግሥት ነው። ለነገሩማ ህወሓት ረሀብንና ድርቅን የፖለቲካ መሣሪያ ማድረጉ በታሪኩ አዲስ ነገር አይደለም። ቀደም ሲል ጫካ በነበረበት ወቅት በግብረ-ሠናይ ድርጅቶች በኩል ከለጋሾች ያገኘውን እህልና መድኃኒት በመቸብቸብ የድርቅ ሰለባ የሆነው ኅብረተሰብ በረሀብ ሲረግፍ የወያኔ ሹማምንትና ምርጥ አባላት በልዩ ልዩ ምግቦችና መጠጦች ሲዘባነኑ እንደነበረ በወቅቱ የተዘገበ ዕውነታ ነው።

ከላይ እንደተጠቀስነው፣ ህወሓት/ኢህአዴግ ይህን ረሀብ ለመደበቅ ዳድቶት ነበር ማለታችን ያለ ምክንያት አይደለም። የረሀቡ አነሳስ መታወቅ የጀመረው ቢያንስ ቢያንስ ህወሓት ሁልጊዜ ለሚያጭበረብረው ምርጫ ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት ስለነበረ፣ ህወሓት የሥልጣን መደላደሉ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ረሀቡ በተከሰተባቸው በተለይ የአፋር፣ የኦሮምያና የደቡብ አካባቢዎች የቤት እንስሳት ሲሞቱና የምግብ ዋጋ ጣሪያ ሲነካ፣ አደንቋሪ የምርጫ ፕሮፓጋንዳው ላይ አትኩሮ እንደነበር እውን ነበር። ወደ አፋር የተሰማሩ የከባድ ጭነት አሽከርካሪ ሾፌሮችና ሌሎችም ያነሷቸውን የሞቱ ግመሎችና ፍየሎች ፎቶዎችና ሌሎች ምስሎች እያጋለጡት ሲመጡና የከተማው ኗሪ ሕዝብ በየቤተክርስቲያናቱና በየመስጊዶች ምህላ ሲይዝ፣ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝና የረሀቡን ስፋትና ጥልቀት ለማመን ተገደደ። ስለሆነም፣ የህወሓት ሸሪክ ለሆኑ ምዕራባውያን መንግሥታትና የመገናኛ ብዙሃን የድርቁ ሁኔታ አስቸጋሪ ፈተና ሆነባቸው። እስካሁን ህወሓት በኢትዮጵያ ያመጣውን ልማት ሳይታክቱ በሚያማምሩና በአሸበረቁ ቃላት "በዓለም ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከሚያሳዩት አገሮች አንደኛዋ፣ የነዳጅ ሀብት ከሌላቸው አገሮች ውጭ በዕድገት የመጀመሪያዋ"...ወዘተ እንዳላሉ ሁሉ አሁን ስለድርቁና ረሀቡ ለማውራት ማጣፊያው ስላጠረባቸው በዋነኛ ተከሳሽነት የክስ ፋይል የተከፈተባት ኤል ኒኞ ሆነች፤ በምትፈጥረው የውቅያኖስ የሙቀት ማዕበል ምክንያት በሚከሰተው የዝናብ እጥረት ነው ተብሏል። ስለዚህም ስለዘንድሮ የኢትዮጵያ ረሀብ አብዛኛዎቹ ሲጽፉ" ኤል ኒኞ ኢትዮጵያን አጠቃች!" የሚል ርዕስ እያስያዙ ሆኗል ።

ይህንን ዓይነት የጋዜጠኝነት ሙያ ስናይ፣ ጆናታን ዲምልቢይ ዘንድሮ የት አለ? የሚያሰኝ ጊዜ ላይ ደርሰናል። እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ ጆናታን በንጉሡ ጊዜ የተደበቀውን ረሀብ ለዓለም ሕዝብ ካጋለጡትና ረሀብተኛው ሕዝብ የእህል ዕርዳታ እንዲያገኝ ከረዱት ጋዜጠኞች ግምባር ቀደሙ ነበር። አብዛኞቹ የዘንድሮዎቹ ጋዜጠኞች ግን አገርን/ሕዝብን ላላማከለ የግለሰቦችና የቡድኖች “ልማት” ልማታዊ ጋዜጠኞች ሆነው ጋዜጠኝነትን ያህል ክቡር ሙያ ሲያራክሱት ይታያሉ።

ተፈጥሮን ምክንያታዊ አድርጎ ከመንግሥታዊ ኃላፊነት ለመሸሽ መሞከር ለኢትዮጵያ መንግሥታት አዲስ ነገር እንዳልሆነ ከላይ አውስተናል። በንጉሡ ጊዜ በ1965 ዓ. ም ለታየው ረሀብ "ወሎ መራቡ አዲስ አይደለም" የሚሉ ባልሥልጣኖች እንደነበሩ ሁሉ፣ ከ12 ዓመታት በኋላ በደርግ ጊዜ በተከሰተው ረሀብ ደግሞ "አድሃሪያንን በቁጥጥራችን ሥር እንዳደረግን፣ ተፈጥሮንም በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን" በማለት ሲኩራራ የነበረው ደርግ ረሀቡ ሲከሰት "ተፈጥሮ ፊቷን አዞረችብን" ነበር ያለው።

ዛሬ ግን ተጠያቂዋ የፈረደባት ኤል ኒኞ ሆናለች። በርግጥ የአየር ጠባይ መለዋወጥ የነበረ፣ ያለና ወደፊትም የሚኖር የተፈጥሮ ክስተት ነው። በተለይ ባለፉት በርካታ ዓመታት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ከመጠን ያለፈ ዝናብ በመጣሉ የጎርፍና አደጋን ሲያስከትል፣ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ዝናብ ከነጭራሹ ጠፍቶ ረሀብ እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል። ኤል ኒኞ በኢትዮጵያ ዘንድሮ ብቻ አይደለም የገባችው፤ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ጀምሮ ውጤቶቹ በአስከፊ ጎርፍና ድርቅ ተፈራራቂነት ጉዳት አድርሳለች። ለረሀብ የተጋለጡ አርሶ-አደሮች እንደሚናገሩት፣ የዘሩት እህል ዝናብ በወቅቱ ባለማግኘቱ ከአረንጓዴነት ወደቢጫነት፣ ከማደግ፣ ከመፋፋትና ከማፍራት ወደ መጠውለግና ከነአካቴውም የተዘራው ሰብል ጨርሶ በመውደሙ ምርት ጠፍቶ ገበሬዎች የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ሕይወት ለማዳን ሲሉ ያሏቸውን ከብቶች እየሸጡና ባገኙት ገንዘብ እህል እየሸመቱ፣ ሰማይ ሰማዩን እያዩ ፈጣሪያቸውን እየተማጸኑ ያሉበት ወቅት ነው። የሚሸጡ እንስሳት ሲያልቁም የትውልድ ቀያቸውን ለቅቀው እህል ወደሚቸሩበት የመጠለያ ቦታ ይሰደዳሉ።

አገዛዙ በግዱ እንዲያምን የተደረገውን የድርቅ ሁኔታ ለመቋቋም ለምኖ ባገኘው ገንዘብ እየገዛ ያለውን በመቶ ሺዎች ቶን የሚገመት ስንዴ ማስገቢያና ማራገፊያ የወደብ ችግር እንደሚገጥመው ብዙዎች እየተነበዩ ነው። በህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ችግሮች እንዴት የተወራረሱና የተሳሰሩ ለመሆናቸው ይህ ጉልህ ማስረጃ ነው። ወደብን ያህል የሀገር ሀብት አሳልፎ ሰጥቶ በሌላ አገር ወደብ ለመጠቀም በቀውጢ ሰዓት ችግር ውስጥ መግባትን የመሰለ የሀገር ክህደት ከቶውንም በታሪክ ተከስቶ አያውቅም።

ኢትዮጵያ በተመጽዋችነት ከዓለም ግምባር ቀደም ሥፍራ የያዘችና ከፍተኛውን ድርሻ የምታገኝ አገር ናት። የሰብዓዊ ዕርዳታ ይሁን፣ የልማት ዕርዳታ እንዲሁም 10 ዓመት የሞላው ሴፍቲ ኔት (safety net) የሚባለው የዓለም ባንክ ለደሃ አርሶ-አደሮች ምግብ ለሥራ ፕሮግራም ከሚሰጠው የሚገኘው ድጎማ ኢትዮጵያን የሚስተካከል አገር የለም። ይህንን ችሮታ የሚለግሱት ምዕራባውያንና የገንዘብ ድርጅቶቻቸው ብቻም አይደሉም። ቻይናም የተቻላትን መለገስ ጀምራለች። ይህን ሁሉ ገንዘብ የሚያጋፍፍ አገዛዝ፣ እንዴት ለችግር ቀን ተዘጋጅቶ ሳይገኝ ቀረ? እንዴትስ ረሀቡ ሰውና እንስሳ መጨረስ ሲጀምር "እባካችሁ እርጥባን" ማለት ጀመረ? አስቀድሞ የረሀብ ማስጠንቀቂያ ዘዴ እጠቀማለሁ የሚል አገዛዝ እንዴት ድርቁ ወደ ረሀብ ከመለወጡ በፊት ለሕዝቡ ሳይደርስ ቀረ? የሚሉትና የመሳሰሉት ጥያቄዎች በኤል ኒኞ ሽፋን ታፍነው የሚቀሩ ጥያቄዎች አይደሉም።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር 95 ሚሊዮን መድረሱ ይገመታል። ከዚሁ ውስጥ 15 ሚሊዮን ያህሉ ለረሀብ የተጋለጠ ሆኗል። የሕዝቡ ቁጥር ሲጨምርና የሦስት አኃዝ ሚሊዮኖች ሲሆን፣ ይህ አገዛዝ እንዴት አድርጎ ነው ሕዝባችንን ከረሀብ መጠበቅ የሚችለው? የ"ልማታዊ መንግሥትነት" ፕሮፓጋንዳና ምዕራባውያን ያዋቀሩት የኢትዮጵያ የዕድገት የይስሙላ አኃዞች ሕዝባችንን ከረሀብና ከጠኔ የኑሮ ስቃይ ለዘለቄታው ከቶውንም አይገላግሉትም። ሕዝባችንን ከዚህ የረሀብ ችግር፤ ከመከራና ከስቃይ መገላገል እንችላለንን? አልፎ ተርፎስ <u>ረሀብን ወደፊት የድሮ ዘመን ታሪክ ማድረግ ይቻላልን?</u> መልሱ "አዎ! እንዴታ!" ነው። ረሀብን ከኢትዮጵያ ምድረ-ገፅ እስከመጨረሻው ለማጥፋትና አገራችንን ከተመጽዋችነት ወደ ለጋሽነት ለመለወጥ የማንችልበት ምክንያት

ከቶውንም ሊኖር አይገባም! ለዚህም ተግባራዊነት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል እንላለን።

1ኛ) ሰማኒያ አምስት በመቶው (85%) የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የተመሠረተው በእርሻ ላይ ነው። በመሆኑም በድርቅ ወቅት በቅድሚያ ተጎጂው ክፍል አርሶ-አደሩ ነው። የእርሻ ምርትን ያለገበሬው ሙሉ ተሳትፎ ማሳደግ አይቻልም። ስለዚህ ይህንን እርሻን ያማከለን ክፍለ-ኤኮኖሚ ለማሳደግ እንዲቻል መሠረታዊ የመሬት ይዞታ ለውጥ ማድረግን ይጠይቃል። አምራቹ ገበሬ በየሚያርሰው መሬት ላይ የይዞታ ባለቤትነቱ በህግ እንዲረጋገጥለትና ምርቱን ለማሳደግ የሚረዱትን ግብዓቶች (ምርጥ ዘር፤ ማዳበሪያ...ወዘተ) በማቅረብና በዝቅተኛ ዋጋ በማከፋፈል እርዳታ እንዲያደርግለት ይገባል። ገበሬው በሚያርሰው መሬት ላይ የይዞታ ባለቤትነቱ ከተረጋገጠለትና የኔነት ከተሰማው እንዲሁም ምርቱንም በሚፈልገው አካባቢ በነፃነት ተንቀሳቅሶ የመሸጥ መብቱ ከተከበረለት መሬቱን ለመንከባከብና ምርቱን ለማሳደግ ማንኛውንም ተግባር ያከናውናል። ከዚህ በተጨማሪ የእርሻ ምርትን ለማሳደግ በባለሙያተኞች የተነደፈ ዕቅድ እንዲወጣና ከትንንሽ የቤተሰብ እርሻዎች ወደ ዘመናዊ ትልልቅ የግል ባለሀብቶችና የመንግሥት እርሻዎች መለወጥን መሠረት የአደረገ የእርሻ ፖሊሲ ማዋቀር፤

2ኛ) ከላይ በአንድ ቁጥር የሠፈረውን እውን ለማድረግ፣ ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን የግድ ይላል። ጠበብቶችና ባለሙያዎች በግልጽ፤ ያለመሸማቀቅና መንግሥትን ባለመፍራት በሚያደርጉት ውይይት፣ ምርምርና የሃሳብ ልውውጥ፣ ተቀባይነት ያላቸውና ጠቃሚ የሆኑ የእርሻና የኤኮኖሚ ዕቅዶች ማውጣትና ተግባራዊ ማድረግ፤

3ኛ) በአገራችን ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ሲኖር፣ አሁን አገሪቱን እያራቆተ ያለው የምሁራን ፍልሰት (brain drain) ይቆማል፤ ከአገራቸው በፖለቲካ ምክንያት የወጡ ጠበብቶችና ባለ ሀብቶች ሁሉ ተመልሰው አገራቸውን የሚያገለግሉበት በር ይከፈታል፤

4ኛ) ነፃ የመገናኛ ብዙሃን መኖርንም የግድ ይላል። ነፃ የመገናኛ ብዙሃን ሲኖሩ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖችን ሙስና፣ ንቅዘትና ወስላታነት በማስረጃ በተደገፉ ዘገባዎች ያለማመንታት ስለሚያጋልጡ፣ ሕዝቡ በአገሩ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናል፤ ባያቸው

ጉድለቶች ላይ እርማት እንዲደረግ መንግሥት ላይ ጫና የማድረግ አቅምም ይኖረዋል። ባለሥልጣናቱም፣ የሕዝቡን አወንታ ካላገኙ በሥልጣን የመቀጠል፣ ወይም እንደገና የመመረጥ ዕድል እንደማይኖራቸው ስለሚያውቁ፣ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ይተጋሉ። ነፃ ጋዜጠኞች ልማታዊ ጋዜጠኞች የማያደርጉትን ረሀብ ገና ሲያንዣብብ ሕዝብና መንግሥት እንዲያውቁት ጥሪ ያሰማሉ። ከወዲሁ ቅድመ-ዝግጅቶች መደረጋቸውንም ያረጋግጣሉ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በአገራችን በኢትዮጵያ ረሀብንና ድርቅን ደግሞ ደጋግሞ ማየቱ አይቀሬ አሳዛኝ እውነታ ይሆናል። በለማኝነታችን የታወቅን ምፅዋተኞች እንደሆንንም እንቀጥላለን። ሕዝባችንም፣ በተለይም አርሶ-አደሩና አርብቶ-አደሩ እንደተጠቃ ይኖራል።

አገራችን ከድህነት ፈሰሰ የምትወጣውና ሁልጊዜ የውጭ እጅ አይታ ከመኖር የምትላቀቀው ለሕዝብና ለሀገር የሚያስብ ዴሞራሲያዊ መንግሥት ሲኖራት ነው። አምራች ኃይል ዕውቀቱንና ገንዘቡን አውጥቶ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ተንቀሳቅሶ ማምረት ሲችል፤ አድሏዊነት ሲጠፋ ሕዝባችን በልቶ ማደር ይችላል። ስለዚህም ለዴሞራሲና ለእኩልነት የምናደረገውን ትግል ከዳር ለማድረስ ሁሉም የተቃዋሚ ኃይሎች በአንድነት ቆመው ለሕዝብ ደንታቢስ የሆነውን የሀወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በሕዝብ ትግል ከሥልጣን ለማውረድ ተባብረን መታገል ይገባናል። የአንድነት ኃይሎች ሁሉ በአንድነት ቆመን እንድንታገል የኢሕአፓ (አንድነት) ዛሬም የአንድነት ጥሪውን ያቀርባል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!